የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር

# AFRICAN CHARTER ON HUMAN AND PEOPLE'S RIGHTS (ACHPR)

## መግቢያ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል የሆኑና "የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር" የተሰኘውን ይህን የስምምነት ሰነድ ፈርመው የተቀበሉ የአፍሪካ ሀገራት፡-

ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሰዎችንና የሕዝቦችን መብቶች ለማራመድና ለመጠበቅ የሚያስችሉ አካላት እንዲቋቋሙ በሚያደርገው በአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ቻርተር የመጀመሪያ ረቂቅ አዘገጃጀት ላይ ለመነጋገር የመንግሥታት መሪዎች ጉባኤ እ.ኤ.አ. ከጁላይ 17 እስከ 20 ቀን 1979 ድረስ በላይቤሪያ ዋና ከተማ በሞኖሮቪያ ባደረገው አሥራ ስድስተኛው መደበኛ ስብሰባ በቁጥር 115(XVI) ያሳለፈውን ውሳኔ በማስታወስ፤

"ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትሕና ሰብአዊ ክብር የአፍሪካ ሕዝቦችን ትክክለኛ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችሉ የዓላማችን መሰረቶች ናቸው" በማለት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር የደነገገውን በመገንዘብ፤

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለተመሰረተበት ቻርተርና ለሁሉ-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ መግለጫ ትኩረት በመስጠት ማንኛውንም ዓይነት ቅኝ ተገዢነት ከአፍሪካ ለማጥፋት፣ የአፍሪካ ሕዝቦች የተሻለ ሕይወት እንዲመሩ ለማስቻል የሚደረገውን ትብብርና ጥረት ለማቀናጀትና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግና ዓለም አቀፍ ትብብርን ለማራመድ በዚሁ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የገቡትን ቃል እንደገና በማረጋገጥ፤

በሰዎችና በሕዝቦች መብቶች መሰረተ ሃሳብ ላይ የሚኖራቸውን አመለካከት በማጎልበት አመልካች ሊሆኑ ለሚገባቸው ታሪካዊ ባህላቸው ገናናነትና አፍሪካዊ ሥልጣኔ ላስገኛቸው እሴቶች ግምት በመስጠት፤

በአንድ በኩል ዓለም አቀፋዊ ጥበቃ የሚያሻቸው ሰብአዊ መብቶች ከሰው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ የመነጨ መሆናቸውንና በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቦች መብቶች የሚገኙበትን ሁኔታ አገናዝቦ ማክበር ለሰብአዊ መብቶች መከበር ዋስትና የሚያስገኝ መሆኑን በመገንዘብ፤

በመብትና በነጻነት መጠቀም በማንኛውም ሰው ላይ ግዴታን የሚያስከትል መሆኑን ከግምት በማስገባት፤

ከዚህ በኋላ ለልማት መብት የተለየ ትኩረት መስጠት ተገቢ መሆኑንና የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች በፅንሰ ሃሳብም ሆነ በዓለም አቀፋዊ ይዘታቸው ከኢኮኖሚ፣ ከሶሻልና ከባህል መብቶች ሊነጠሉ የማይችሉ መሆናቸውንና የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል መብቶችን ማክበር በሲቪልና በፖለቲካ መብቶች ለመጠቀም ዋስትና መሆኑን በማመን፤

ሕዝቦቿ ለክብራቸውና ለእውነተኛ ነጻነት አሁንም በትግል ላይ የሚገኙበትንና ቅኝ ተገዥነትን፣ የእጅ አዙር ቅኝ ተገዥነትን፣ የዘር አድልዎን፣ ጽዮናዊነትን ለማጥፋትና የውጭ ኃይል ወታደራዊ ሠፈሮችንና ማንኛውንም ዓይነት አድልዎን በተለይም በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አመለካከት ላይ የተመሰረተ አድልዎን ለመደምሰስ ቆርጠው የተነሡበትን አፍሪካን ሙሉ በሙሉ ነጻ ለማውጣት ያለባቸውን ኃላፊነት በማወቅ፤

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የገለልተኛ ሀገራት ንቅናቄና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተቀበሏቸው መግለጫዎች፣ ስምምነቶችና ሌሎች ሰነዶች በተካተቱት የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችና ነጻነቶች መርሆዎች መሰረት የገቡትን ቃል እንደገና በማረጋገጥ፤

በአፍሪካ ባህል ለእነዚህ መብቶችና ነጻነቶች መከበር የሚሰጠውን ክብር ከግምት በማስገባት የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችንና ነጻነቶችን ለማራመድና ለማክበር ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በጥብቅ በማመን፤

ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተስማምተዋል፤

# ክፍል 1

## መብቶችና ግዴታዎች

### ምዕራፍ -1- የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች

#### አንቀጽ 1

ይህን ቻርተር ፈርመው የተቀበሉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት በዚህ ቻርተር የተደነገጉትን መብቶች፣ ግዴታዎችና ነጻነቶች አውቀው በመቀበል ለተግባራዊነታቸው ሕግ ለማውጣትና ሌሎች እርምጃዎችን ለመውሰድ ግዴታ ገብተዋል፡፡

#### አንቀጽ 2

ማንኛውም ሰው በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አስተሳሰብ፣ በብሔርና በማኅበራዊ ምንጭ፣ በሀብት፣ በመወለድ ወይም በሌላ ሁኔታ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ ቻርተር ዕውቅናና ዋስትና ያገኙት መብቶችና ነጻነቶች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

#### አንቀጽ 3

1. ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው፡፡
2. ማንኛውም ሰው እኩል የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

#### አንቀጽ 4

ሰዎች በተፈጥሮ ክቡራን ናቸው፤ ማንኛውም ሰው ሕይወቱና አካላዊ ክብሩ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው፤ ይህን መብቱንም በዘፈቀደ አይገፈፍም፡፡

#### አንቀጽ 5

ማንም ሰው በተፈጥሮ የታደለው ሰብአዊ ክብርነቱ እንዲከበርለትና ሕጋዊ ይዞታውም እንዲታወቅለት መብት አለው፡፡ ማንኛውም ብዝበዛና ውርደት፤ በተለይም ባርነት፣ የባርነት ንግድ፣ አሰቃይ፣ የጭካኔ፣ ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ ቅጣትና አያያዝ የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

#### አንቀጽ 6

ማንኛውም ሰው ነጻነቱና አካላዊ ደኅንነቱ ተጠብቆለት የመኖር መብት አለው፡፡ ቀድሞ በሕግ በተደነገጉት ሁኔታዎችና ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ነጻነቱን እንዲያጣ ሊደረግ አይችልም፡፡ በተለይም ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር ወይም ሊያዝ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 7

1. ማንም ሰው በደሉ እንዲሰማለት የማድረግ መብት አለው፤ ይህም፦
   ሀ/ ጸንተው በሚገኙ ስምምነቶች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና ልማዶች ዕውቅና ያገኙና ዋስትና የተሰጣቸው መሰረታዊ መብቶቹን የሚጥሱ ድርጊቶች ሲፈጸሙበት ሥልጣን ላላቸው ብሔራዊ አካላት አቤቱታ የማቅረብ መብትን፤
   ለ/ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ አካል ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ጥፋተኛ ተደርጎ ያለመወሰድ መብትን፤
   ሐ/ ራሱ በመረጠው አማካሪ አማካይነት መከራከርን ጨምሮ የመከላከል መብትን፤ እና
   መ/ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ አድሎአዊ ባልሆነ ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ አካል የመዳኘት መብትን ያካትታል።
2. ማንም ሰው በተፈጸመበት ወይም ሳይፈጸም በቀረበት ጊዜ በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል ያልሆነውን ድርጊት በመፈጸሙ ወይም ሳይፈጽም በመቅረቱ ሊቀጣ አይችልም፤ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ያልተደነገገው ቅጣትም አይወሰንበትም። ቅጣት ግላዊ በመሆኑ የሚፈጸመውም በአጥፊው ላይ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 8

ማንም ሰው የኅሊና፣ የሙያና እምነትን በነጻነት የመከተል ነጻነት ዋስትና ተሰጥቶታል፤ በሕግና በሥርዓት ካልሆነ በስተቀር በእነዚህ ነጻነቶች እንዳይጠቀም ገደብ አይደረግበትም።

## አንቀጽ 9

1. ማንኛውም ሰው መረጃ የማግኘት መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው ሕግን ተከትሎ ሃሳቡን የመግለጽና የማሠራጨት መብት አለው።

## አንቀጽ 10

1. ማንኛውም ሰው ሕግን አክብሮ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው።
2. በአንቀጽ 29 በተደነገገው መሰረት የአንድነት የመተባበር ግዴታን ለመወጣት ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው የአንድ ማኅበር አባል እንዲሆን አይገደድም።

## አንቀጽ 11

ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በነጻ ለመሰብሰብ መብት አለው፤ በዚህ መብት አጠቃቀም ላይ በሕግ በተለይም ብሔራዊ ጸጥታን፣ የሕዝብ ደኅንነትን፣ ጤናን፣ ሥነ ምግባርንና የሌሎችን መብትና ነጻነት ለማስከበር በሚወጣ ሕግ ብቻ አስፈላጊ ገደቦች ሊደረጉ ይችላሉ።

## አንቀጽ 12

1. ማንኛውም ሰው የሚኖርበትን ሀገር ሕግ በማክበር የመንቀሳቀስና በፈለገው ቦታ የመኖር መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው የራሱን ሀገር ጨምሮ ከማንኛውም ሀገር የመውጣትና ወደራሱ ሀገርም ተመልሶ የመግባት መብት አለው። የዚህ መብት አጠቃቀም ብሔራዊ ጸጥታን፣ ሕግንና ሥርዓትን፣ የሕዝብ ጤናን ወይም ሞራልን ለመጠበቅ በሚወጣ ሕግ ብቻ ሊገደብ ይችላል።
3. ማንኛውም ሰው የማሳደድ ድርጊት በሚፈጸምበት ጊዜ የሀገራቱ ሕጎች እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚደነግጉት መሰረት በሌሎች ሀገራት ጥገኝነት የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።
4. ዜግነት ሳይኖረው ይህን ቻርተር ፈርሞ በተቀበለ ሀገር እንዲገባ በሕግ የተፈቀደለት ሰው ከዚህ ሀገር እንዲወጣ የሚደረገው በሕግ መሰረት በሚሰጥ ውሳኔ ነው።
5. ዜጋ ያልሆኑ ሰዎችን በግፍ ከሀገር ማስወጣት የተከለከለ ድርጊት ነው። በብሔር፣ በዘር ወይም በሃይማኖት ቡድኖች ላይ የተመሰረተ ከሀገር ማስወጣት በግፍ ማስወጣት ተደርጎ ይወሰዳል።

## አንቀጽ 13

1. ማንኛውም ዜጋ ሕግ በሚፈቅደው መሰረት በቀጥታ ወይም በነጻ በመረጣቸው ተወካዮቹ አማካይነት በሀገሩ መንግሥት አስተዳደር የመሳተፍ መብት አለው።
2. ማንኛውም ዜጋ በሀገሩ መንግሥት በሚሰጠው የሕዝብ አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ የመሆን መብት አለው።
3. ማንኛውም ሰው በሕዝብ ንብረትና ለሕዝብ በሚሰጥ አገልግሎት በሕግ ፊት ከሁሉም ሰዎች ጋር እኩል የመጠቀም መብት አለው።

## አንቀጽ 14

የንብረት ባለቤት የመሆን መብት የሕግ ዋስትና አለው፡፡ ሆኖም ይህ መብት ለሕዝብ ፍላጎት ወይም ለአጠቃላይ የሕብረተሰብ ጥቅም ሲባል አግባብነት ባላቸው ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት ሊገደብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 15

ማንኛውም ሰው ፍትሐዊና ተስማሚ በሆኑ ሁኔታዎች የመሥራትና ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ደመወዝ የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 16

1. ማንኛውም ሰው የአካልም ሆነ የአእምሮ ጤንነቱ በሚኖርበት ማኅበረሰብ ሊደረግ በሚችልበት ደረጃ እንዲጠበቅለት የማድረግ መብት አለው፡፡
2. ይህን ቻርተር ፈርመው የተቀበሉ ሀገራት የሕዝባቸውን ጤንነት ለመጠበቅና በሚታመሙበት ጊዜም ሕክምና ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

## አንቀጽ 17

1. ማንኛውም ሰው የመማር መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ማኅበረሰብ ባህላዊ ሕይወት በነጻ የመሳተፍ መብት አለው፡፡
3. በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን መንፈሳዊና ባህላዊ ዕሴቶች ማራመድና መጠበቅ የእያንዳንዱ ሀገር ግዴታ ነው፡፡

## አንቀጽ 18

1. ቤተሰብ የሕብረተሰብ መነሻ መሰረት ነው፡፡ መንግሥትም አካላዊና ሞራላዊ ጤንነቱን በመንከባከብ ጥበቃ ያደርግለታል፡፡
2. መንግሥት በማኅበረሰብ ተቀባይነት ላላቸው መንፈሳዊና ሞራላዊ ዕሴቶች መገኛና መሰረት ለሆነው ለቤተሰብ እርዳታ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

3. መንግሥት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም አድልዎ መጥፋቱንና በተጨማሪም በዓለም አቀፍ መግለጫዎችና ስምምነቶች መሰረት የሴቶችና የሕፃናት መብቶች መጠበቃቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
4. አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች ለአካላዊና ሞራላዊ ፍላጎታቸው የሚስማማ ልዩ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 19

ሁሉም ሕዝቦች እኩል ናቸው፤ እኩል የመከበርና በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡ አንዱ ሕዝብ ሌለውን ሊጫን የሚችልበት ምክንያት በምንም ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡

## አንቀጽ 20

1. ሁሉም ሕዝቦች የመኖር መብት አላቸው፤ የማያጠያይቅና ሊገሰስ የማይችል የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አላቸው፡፡ የራሳቸውን የፖለቲካ አቋም ይወስናሉ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማታቸውን ራሳቸው በነጻነት በመረጡት ፖሊሲ መሰረት ያካሂዳሉ፡፡
2. በቅኝ ተገዢነት ወይም በጭቆና ቀንበር ሥር የሚገኙ ሕዝቦች በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዕውቅና ባገኘ በማንኛውም መንገድ ተጠቅመው ራሳቸውን ከጭቆና አገዛዝ ነጻ የማውጣት መብት አላቸው፡፡
3. ሁሉም ሕዝቦች ራሳቸውን ከውጭ ኃይል የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ወይም የባህል ጭቆና ነጻ ለማድረግ ለሚያካሂዱት ትግል ይህን ቻርተር ፈርመው በተቀበሉ ሀገሮች የመታገዝ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 21

1. ሁሉም ሕዝቦች ንብረታቸውንና የተፈጥሮ ሃብታቸውን በነጻነት ይገለገሉበታል፡፡ በዚህ መብት መገልገል የሚቻለው ለሕዝብ ጥቅም ብቻ ነው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ሕዝብ ይህን መብቱን አይገፈፍም፡፡
2. ከሕግ ውጭ ንብረት የመቀማት ድርጊት ሲፈጸም ሕዝብ ከሕግ ውጭ የተወሰደበትን ንብረት በሕጋዊ መንገድ የማስመለስና ለደረሰበት ጉዳትም ተገቢ ካሳ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

3. በንብረትና በተፈጥሮ ሀብት መገልገል፣ በጋራ መከባበር፣ ፍትሐዊ በሆነ ልውውጥና በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት ሃሳቦች ላይ የተመሰረተ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብርን ለማራመድ የሚኖር ግዴታን የሚቃረን አይሆንም።
4. ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት በግልም ሆነ በአንድነት ይህን በንብረትና በተፈጥሮ ሀብት የመገልገል መብትን የአፍሪካን አንድነትና ትብብር በሚያጠናክር ሁኔታ ይጠቀሙበታል።
5. ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት ሕዝቦቻቸው ከተፈጥሮ ሀብቶቻቸው በሚገኘው ጥቅም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በውጭ ኃይል በተለይም በዓለም አቀፍ ሞኖፖሊስቶች የሚደረገውን ሁሉንም ዓይነት የኢኮኖሚ ብዝበዛ ለማስወገድ ግዴታ ገብተዋል።

## አንቀጽ 22

1. ሁሉም ሕዝቦች የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል ልማታቸው ነጻነታቸውን፣ ማንነታቸውንና የሰው ልጅ የጋራ ቅርስ ተጠቃሚነታቸውን በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዲካሄድ የማድረግ መብት አላቸው።
2. ሀገራት በግልም ሆነ በአንድነት የሕዝብ የልማት (የማደግ) መብት መከበሩን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።

## አንቀጽ 23

1. ሁሉም ሕዝቦች የየሀገሮቻቸውና የዓለም ሰላምና ጸጥታ እንዲጠበቅ የማድረግ መብት አላቸው። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በውስጠ ታዋቂ ያረጋገጣቸውና የአፍሪካ አንድነት ቻርተርም እንደገና ያረጋገጣቸው የአንድነትና የወንድማማችነት ግንኙነቶች መሰረተ ሃሳቦች በሀገራት መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት ይመራሉ።
2. ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት ሰላምን፣ አንድነትና ወንድማማችነትን ለማጠናከር፡-
   ሀ/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ 12 በተደነገገው መሰረት ጥገኝነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በስደት ለቆት በመጣው ሀገር ወይም ይህን ቻርተር በተቀበለ ሀገር ላይ ሰላምን የማናጋት ድርጊት የማይፈጽም መሆኑን፤
   ለ/ የግዛት ክልሎቻቸው ይህን ቻርተር በተቀበለ በማንኛውም ሀገር ሕዝብ ላይ ሰላምን የማናጋት ወይም የሽብር ድርጊት መፈጸሚያዎች እንዳይሆኑ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 24

ሁሉም ሕዝቦች ለልማታቸው ተስማሚ የሆነ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 25

ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት በዚህ ቻርተር የተካተቱትን መብቶችና ነጻነቶች በማስተማር፣ በሥርዓተ ትምህርት በማስገባትና አትሞ በማሠራጨት የማራመድና መከበራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፤ እነዚህ መብቶችና ነጻነቶች አብረዋቸው ከሚሄዱ ግዴታዎች ጋር በሰዎች አእምሮ ሠርጸው የገቡ መሆናቸውንም ያረጋግጣሉ።

## አንቀጽ 26

ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት ፍርድ ቤቶች መደበኛ ሥራቸውን በነጻነት እንዲያከናውኑ ዋስትና የመስጠት ግዴታ አለባቸው። እንዲሁም በዚህ ቻርተር ዋስትና የተሰጣቸውን መብቶችና ነጻነቶች ለማራመድና ለመጠበቅ ኃላፊነት የሚኖራቸውን ተቋማት የማቋቋምና እየተጠናከሩም እንዲሄዱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

## ምዕራፍ 2 - ግዴታዎች

### አንቀጽ 27

1. ማንኛውም ሰው በቤተሰቡ፣ በሚኖርበት ማኅበረሰብ፣ በሀገሩ፣ በሌሎች በሕግ ዕውቅና በተሰጣቸው ማኅበረሰቦችና በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የሚጠበቅበትን የመፈጸም ግዴታ አለበት።
2. እያንዳንዱ ሰው በመብቶቹና በነጻነቶቹ ለመጠቀም የሚችለው የሌሎችን መብት፣ የጋራ ደኅንነት፣ ሞራልንና የጋራ ጥቅምን በማይቃረን ሁኔታ ነው።

### አንቀጽ 28

እያንዳንዱ ሰው ሌላውን ወገኑን ያለምንም ልዩነት የመቀበልና የማክበር ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህም ግዴታ የጋራ መከባበርንና መቻቻልን በማራመድ፣ በመጠበቅና በማጠናከር ላይ ያተኮሩ ግንኙነቶችን መመስረትንና መጠበቅን ይጨምራል።

### አንቀጽ 29

ማንኛውም ሰው በተጨማሪ፡-

1. የቤተሰብ ጤናማ እድገት የመጠበቅና ለቤተሰብ አንድነት መከበር የመቆም፣ ወላጆቹን በማንኛውም ጊዜ የማክበርና ሲቸገሩም የመርዳት፤
2. የሀገሩን ማኅበረሰብ አካላዊ ዐቅሙንና ዕውቀቱን ሳይቆጥብ የማገልገል፤
3. ዜጋ ወይም ኗሪ የሆነበትን ሀገር ጸጥታ አደጋ ላይ የሚጥል ድርጊት ያለመፈጸም፤
4. ማኅበራዊና ብሔራዊ አንድነትን የመጠበቅና የማጠናከር፤
5. በሕግ በሚደነገገው መሰረት ብሔራዊ ነጻነትንና የሀገርን አንድነት የመጠበቅ፣ የመንከባከብና ከጥቃት ለመከላከል የመሰለፍ፤
6. ዐቅሙና ችሎታው በሚፈቅድለት መጠን የመሥራትና የሕብረተሰቡን ጥቅም ለማስከበር የሚጣልበትን ግብር የመክፈል፤
7. ከሌሎች የሕብረተሰቡ አባላት ጋር በሚፈጥራቸው ግንኙነቶች ሁሉ በመቻቻል መንፈስ፣ በውይይትና በምክክር ጠቃሚ የሆኑ የአፍሪካ ባህሎችን የመጠበቅ፣ የመንከባከብና በአጠቃላይም የሕብረተሰቡን ሞራላዊ ደኅንነት ለመንከባከብ የሚፈለግበትን አስተዋጽኦ የማድረግ፤

8. በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ደረጃ ዐቅሙና ችሎታው በሚፈቅድለት መጠን የአፍሪካን ኅብረት ለማራመድና ለማሳካት የሚፈለግበትን አስተዋጽኦ የማድረግ፤ ግዴታ አለበት።

## ክፍል 2

## የአፈጻጸም እርምጃዎች

## ምዕራፍ 1 - የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን

## መቋቋምና መደራጀት

### አንቀጽ 30

የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን በአፍሪካ ለማራመድና መከበራቸውንም ለማረጋገጥ ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራው "የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ኮሚሽን" በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ ተቋቁሟል፡፡

### አንቀጽ 31

1. ኮሚሽኑ በሕግ ሙያ ተገቢው ልምድ ላላቸው የተለየ ግምት በመስጠት በሞራል ጥንካሬያቸው፣ በታማኝነታቸው፣ ከአድልዎ ነጻ በመሆናቸውና በሰዎችና በሕዝቦች መብቶች ላይ ባላቸው ዕውቀት ከሚታወቁ አፍሪካውያን መካከል የተመረጡ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የኮሚሽኑ አባላት አገልግሎት የሚሰጡት በግላቸው ነው፡፡

### አንቀጽ 32

ኮሚሽኑ ከአንድ ሀገር ከአንድ የበለጠ አባላት አይኖሩትም፡፡

### አንቀጽ 33

የኮሚሽኑ አባላት ይህን ቻርተር በተቀበሉ ሀገራት ለምርጫ ከሚቀርቡት ሰዎች መካከል በምሥጢር በሚሰጥ ድምጽ ይመረጣሉ፡፡

### አንቀጽ 34

እያንዳንዱ ይህን ቻርተር የተቀበለ ሀገር ከሁለት ተወዳዳሪዎች በላይ ለምርጫ ሊያቀርብ አይችልም፡፡ ለምርጫ የሚቀርቡት ተወዳዳሪዎች ይህን ቻርተር ከተቀበሉት ሀገራት የአንዱ ዜግነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡ አንድ ሀገር ለምርጫ ያቀረባቸው ተወዳዳሪዎች ሁለት በሚሆኑበት ጊዜ ከሁለቱ ተወዳዳሪዎች አንዱ ለምርጫ ያቀረባቸው ሀገር ዜጋ መሆን የለበትም፡፡

## አንቀጽ 35

1. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት ተወዳዳሪዎችን ለምርጫ እንዲያቀርቡ ቢያንስ የአባላት ምርጫ ከሚደረግበት ከአራት ወራት በፊት ጥሪ ያደርግላቸዋል፡፡
2. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለምርጫ የቀረቡ ሰዎችን ስም በፊደል ተራ በመመዝገብ ቢያንስ ምርጫው ከሚካሄድበት ከአንድ ወር በፊት ለሀገርና ለመንግሥት መሪዎች ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ 36

የኮሚሽኑ አባላት የሚመረጡት ለስድስት ዓመታት የሥራ ዘመን ሲሆን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ምርጫ ከተመረጡት አባላት መካከል የአራቱ አባላት የሥራ ዘመን ከሁለት ዓመታት በኂላ የሚያበቃ ሲሆን የሦስቱ አባላት ዘመን ደግሞ አራት ዓመት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 37

የአባላት ምርጫ ከተካሄደ በኂላ ወዲያውኑ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ሊቀመንበር ከላይ በአንቀጽ 36 በተደነገገው መሰረት የሚመረጡትን አባላት ስም በዕጣ ይወስናል፡፡

## አንቀጽ 38

ምርጫ ከተደረገ በኂላ የኮሚሽኑ አባላት ግዴታቸውን ያለምንም አድልዎና ታማኝነት የሚወጡ መሆናቸውን ቃል በመግባት ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 39

1. አንድ የኮሚሽኑ አባል ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወይም ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ጉዳዩን ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ወዲያውኑ ያሳውቃል፤ ዋና ጸሐፊውም ይኸው የአባልነት ቦታ አባሉ ከሞተበት ወይም በፈቃዱ ሥራውን ከለቀቀበት ቀን ጀምሮ ክፍት መሆኑን ይገልጻል፡፡
2. አንድ የኮሚሽኑ አባል በጊዜያዊነት ሳይሆን ለዘለቄታው ግዴታውን መወጣቱን አቋርጧል ብለው ቀሪ የኮሚሽኑ አባላት የሚያምኑ ከሆነ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር

ሁኔታውን ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ያሳውቃል፤ ዋና ጸሐፊውም ቦታው ክፍት መሆኑን ይገልጻል፡፡

3. ከላይ በተገለጸው መሰረት በተፈጠረው በእያንዳንዱ ሁኔታ ከኮሚሽኑ አባልነት የለቀቀው አባል ቀሪ የሥራ ዘመን ከስድስት ወራት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ በቀሪው የሥራ ዘመን የሚያገለግል አባል መርጦ ይተካል፡፡

## አንቀጽ 40

እያንዳንዱ የኮሚሽኑ አባል ተተኪው ኃላፊነቱን እስኪረከበው ድረስ ኃላፊነቱን እንደያዘ ይቆያል፡፡

## አንቀጽ 41

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የኮሚሽኑን ጸሐፊ ይሾማል፡፡ ኮሚሽኑ ሥራውን በሚገባ ለማከናወን እንዲችል አስፈላጊ ሠራተኞችን ይመድባል፤ አስፈላጊውን አገልግሎት እንዲያገኝም ያደርጋል፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም ለሚመደቡ ሠራተኞችና ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስፈልገውን ወጪ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 42

1. ኮሚሽኑ ለሁለት ዓመታት የሥራ ዘመን የሚያገለግሉ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣል፡፡ ሊቀመንበሩና ምክትል ሊቀመንበሩም የሥራ ዘመናቸው ካለቀ በኋላ እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡
2. ኮሚሽኑ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡
3. ከኮሚሽኑ አባላት መካከል ሰባት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
4. ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
5. ዋና ጸሐፊው ኮሚሽኑ በሚያደርገው ስብሰባ ሊገኝ ይችላል፤ ነገር ግን በሚደረገው ውይይት ለመካፈል ወይም ድምፅ ለመስጠት አይችልም፡፡ ሆኖም የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ሃሳቡን እንዲገልጽ ሊጋብዘው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 43

የኮሚሽኑ አባላት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ልዩ ጥቅምንና ከተጠያቂነት ነጻ መሆንን አስመልክቶ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት በጸደቀው ስምምነት መሰረት ልዩ ጥቅም ያገኛሉ ከተጠያቂነትም ነጻ ይሆናሉ፡፡

ለኮሚሽኑ አባላት የሚደረጉ ክፍያዎችና አበሎች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት መደበኛ በጀት ይካተታሉ፡፡

## ምዕራፍ 2 - የኮሚሽኑ ሥልጣን

## አንቀጽ 45

ኮሚሽኑ የሚከተለው ሥልጣን አለው፤

1. የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ማራመድ፤ በተለይም
   ሀ/ ሰነዶችን ማሰባሰብ፣ በሰዎችና በሕዝቦች መብቶች ላይ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ሴሚናሮችን፣ ሲምፖዚየሞችንና ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀት፣ መረጃዎችን ማስተላለፍ፣ ለሰዎችና ለሕዝቦች መብቶች መጠበቅ ትኩረት የሚሰጡ ብሔራዊና አካባቢያዊ ተቋሞችን ማበረታታትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥታት ማቅረብ፤
   ለ/ የአፍሪካ መንግሥታት ለሚያወጧቸው ሕጎች መሰረት በሚያደርጓቸው የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን ሊያቃልሉ የሚችሉ ደንቦችንና መመሪያዎችን መቅረጽና ማውጣት፤
   ሐ/ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ለማራመድና ለማስከበር ከተቋቋሙ አፍሪካዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር መተባበር፤
2. በዚህ ቻርተር በተደነገገው ሁኔታ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ፤
3. ይህን ቻርተር በተቀበለ ሀገር፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አካል በሆነ ድርጅት ወይም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዕውቅና በተሰጠው ሌላ ድርጅት ጥያቄ ሲቀርብለት የዚህን ቻርተር ድንጋጌዎች መተርጎም (ማብራሪያ መስጠት)
4. በሀገርና በመንግሥት መሪዎች ስብሰባ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን

## ምዕራፍ 3 - የኮሚሽኑ የአሠራር ሥነ ሥርዓት

### አንቀጽ 46

ኮሚሽኑ ምርመራ ሲያካሂድ ማንኛውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ዘዴ ይጠቀማል፤ ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ወይም ከሌላ ማብራሪያ ለመስጠት ከሚችል ሌላ ሰው ማብራሪያ ለመቀበል ይችላል፡፡

## ከሀገራት የሚቀርቡ ክሶችና ጥቆማዎች

### አንቀጽ 47

አንድ ይህን ቻርተር የተቀበለ ሀገር ይህን ቻርተር የተቀበለ ሌላ ሀገር የቻርተሩን ድንጋጌዎች የሚጥስ ድርጊት ፈጽሟል የሚል እምነት ሲኖረው ለተፈጸመው ድርጊት ማብራሪያ እንዲሰጠው በጽሑፍ ሊጠይቀው ይችላል፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊና የኮሚሽኑ ሊቀመንበርም ጉዳዩን እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡ ጥያቄው የቀረበለት ሀገርም ጥያቄው በደረሰው በሦስት ወራት ውስጥ ጉዳዩን በግልጽ የሚያብራራ የጽሑፍ መግለጫ ጥያቄውን ላቀረበው ሀገር ይሰጣል፡፡ ይህ መግለጫ በተቻለ መጠን ተፈጻሚ የሆኑና ሊሆኑ የሚችሉ ሕጎችንና የአሠራር ደንቦችን የሚያብራሩ መረጃዎችንና የተወሰዱ ወይም ሊወሰዱ የሚችሉ የመፍትሔ እርምጃዎችን የሚያካትት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 48

ጥያቄው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ ሁለቱ ሀገራት በጋራ በሚያደርጉት ውይይት ወይም በሌላ ሰላማዊ መንገድ ጥያቄው በቀረበለት ሀገር ለጉዳዩ መፍትሔ የማይገኝለት ከሆነ ከሁለቱ ሀገራት አንዱ ጉዳዩን በኮሚሽኑ ሊቀመንበር አማካይነት ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይችላል፤ ሌላው ሀገርም እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ 49

በአንቀጽ 47 በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢሆንም፤ አንድ ይህን ቻርተር የተቀበለ ሀገር ቻርተሩን የተቀበለ ሌላ ሀገር በቻርተሩ የተደነገገውን የሚጥስ ድርጊት ፈጽሟል ብሎ ሲያምን አድራሻውን ለኮሚሽኑ ሊቀመንበር፣ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊና ድርጊቱን ፈጽሟል ለሚለው ሀገር በማድረግ ጉዳዩን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 50

ኮሚሽኑ ጉዳዩ ሲደርሰው ተቀብሎ የራሱን እርምጃ የሚወስደው ድርጊቱን ፈጽሟል በተባለው ሀገር ተፈጸመ ለተባለው ድርጊት መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ካለ፣ በሥርዓቱ ተጠቅሞ መፍትሔ ለመስጠት ከመጠን ያለፈ ረዥም ጊዜ ይወስዳል የሚል እምነት ከሌለው በስተቀር በሀገሩ መፍትሔ ለማግኘት ማናቸውም ሕጋዊ እርምጃዎች ሁሉ ተወስደው ያልተሳካ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

## አንቀጽ 51

1. ኮሚሽኑ የቻርተሩን ድንጋጌዎች የሚጥስ ድርጊት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ የቀረበበት ሀገር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ ክሱን በሚመረምርበት ጊዜ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት በኮሚሽኑ ፊት የሚወክሏቸውን መርጠው በክሱ ላይ ያላቸውን አቋሞች በጽሑፍ ወይም በቃል ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 52

ኮሚሽኑ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሀገራትና ከሌሎች ምንጮች አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መረጃዎች ካገኘና በሰዎችና በሕዝቦች መብቶች መከበር ላይ የተመሰረተ አግባቢ መፍትሔ ለማግኘት ተገቢ በሆኑ መንገዶች ከተጠቀመ በኋላ በአንቀጽ 48 በተደነገገው መሰረት ሁኔታውን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ በምርመራው የደረሰበትንና ያገኘውን ፍሬ ነገር የያዘ መግለጫ ያዘጋጃል፡፡ ይህ መግለጫም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሀገራትና ለሀገርና ለመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ይላካል፡፡

## አንቀጽ 53

ኮሚሽኑ መግለጫውን በሚልክበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት ለሀገርና ለመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 54

ኮሚሽኑ የሥራ እንቅስቃሴውን የሚመለከት ሪፖርት ለእያንዳንዱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል፡፡

## ሌሎች ክሶችና ጥቆማዎች

## አንቀጽ 55

1. የኮሚሽኑ ጸሐፊ እያንዳንዱ ስብሰባ ከመደረጉ በፊት ቻርተሩን ከተቀበሉ ሀገራት ውጭ ለኮሚሽኑ የቀረቡትን ክሶች ጥቆማዎች ዝርዝር ለኮሚሽኑ አባላት ያስተላልፋል፤ የኮሚሽኑ አባላትም ከቀረበላቸው ዝርዝር ውስጥ መታየት የሚኖርባቸውን ክሶች ጥቆማዎች ይመርጣሉ፡፡
2. አንድ ጥቆማ በኮሚሽኑ የሚታየው የኮሚሽኑ አባሎች በድምጽ ብልጫ ሲወስኑ ነው፡፡

## አንቀጽ 56

ኮሚሽኑ በአንቀጽ 55 በተደነገገው መሰረት የተቀበላቸውን የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን የሚመለከቱ ጥቆማዎች፤

1. ስማቸው እንዳይገለጽ ቢጠይቁም ጥቆማዎቹ አቅራቢዎችን የሚያመለክቱ ከሆነ፤
2. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርንና ይህን ቻርተር የማይቃረኑ ከሆነ፤
3. ጥቆማ በቀረበበት ሀገርና በተቋሞቹ ወይም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ላይ በተነጣጠሩ አጸያፊና የስድብ ቃላት ያልተጻፈ ከሆነ፤
4. በመገናኛ ብዙኃን በተላለፉ ዜናዎች ብቻ የተመሰረቱ ካልሆኑ፤
5. ተፈጽሟል ለተባለው ድርጊት ክሱ በቀረበበት ሀገር መፍትሔ ሊያስጥ የሚችል የአሠራር ሥርዓት ካለ፤ በሥርዓቱ ተጠቅሞ መፍትሔ ለማግኘት ከመጠን ያለፈ ረዥም ጊዜ ይወስዳል ካልተባለ በስተቀር በሀገር ውስጥ አስፈላጊ እርምጃዎች ሁሉ ተወስደው መፍትሔ ባለመገኘቱ የተላኩ ከሆኑ፤
6. በሀገር ውስጥ መፍትሔ ለማግኘት አስፈላጊ እርምጃዎች ከተወሰዱ ወይም ኮሚሽኑ ጉዳዩን ከተረዳበት ቀን በኋላ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ የቀረቡ ከሆኑ፤
7. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተመሰረተበት ቻርተር፤ ወይም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በተመሰረተበት ቻርተር፣ ወይም በዚህ ቻርተር በተደነገጉት መርሆዎች መሰረት መፍትሔ ባስገኙላቸው ችግሮች ላይ ያልተመሰረቱ ከሆኑ ጥቆማዎቹን ያያል፤ ይመረምራል፡፡

## አንቀጽ 57

ሁሉም ጥቆማዎች የያዟቸው ፍሬ ነገሮች ከመታየታቸውና ከመመርመራቸው በፊት በኮሚሽኑ ሊቀመንበር አማካይነት ጥቆማዎቹ የቀረቡበት ሀገር እንዲያውቃቸው ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 58

1. የቀረቡት ጥቆማዎች በኮሚሽኑ ሲታዩና ሲመረመሩ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን በተከታታይ በከፍተኛ ደረጃና በገፍ የጣሱ ድርጊቶች መፈጸማቸውን የሚያጋልጡ ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚጠቁሙ ከሆነ ኮሚሽኑ እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ እንዲገነዘብ ያደርጋል፡፡
2. የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ኮሚሽኑ ጉዳዮችን በጥልቀት በመመርመር ትክክለኛውን ሁኔታ የሚገልጽ ሪፖርት ከምርመራው ውጤትና የውሳኔ ሃሳብ ጋር እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. ኮሚሽኑ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስገድድ ጉዳይ መኖሩን የተገነዘበ እንደሆነ ሁኔታውን ጉዳዩ በጥልቀት እንዲመረመር ለጠየቀው የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ሊቀመንበር ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 59

1. በዚህ ቻርተር ድንጋጌዎች መሰረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆኑ እስኪወስን ድረስ በምስጢር እንደተያዙ ይቆያሉ፡፡
2. ሆኖም የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ሲወስን ሪፖርቱ ሊታተም ይችላል፡፡
3. በኮሚሽኑ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚዘጋጀው ሪፖርት የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ካየውና ከመረመረው በኋላ በኮሚሽኑ ሊቀመንበር እንዲታተም ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ 4 - አግባብነት ያላቸው (ተፈጻሚ የሚሆኑ) መርሆዎች

### አንቀጽ 60

ኮሚሽኑ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ለማስከበር የወጡ ዓለም አቀፍ ሕጎች፤ በተለይም የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ለማስከበር የወጡ ሰነዶች ድንጋጌዎች፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ድንጋጌዎች፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር ድንጋጌዎች፤ ሁሉ-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ድንጋጌዎች የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን ለማስከበር በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካውያን ሀገራት ተቀባይነት ያገኙ የሌሎች ሰነዶች ድንጋጌዎችና እንዲሁም ይህን ቻርተር የተቀበሉ ሀገራት አባላት በሆኑባቸው ለልዩ ተልዕኮ በተቋቋሙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ተቀባይነት ያገኙ ልዩ ልዩ ሰነዶች ድንጋጌዎች ያካተቷቸውን ፅንሰ ሃሳቦች ለዚህ ቻርተር ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይገለገልባቸዋል፡፡

### አንቀጽ 61

ኮሚሽኑ ለቻርተሩ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አግባብነት ያለውን የሕግ መርሕ ለመወሰን ለሚወስዳቸው አጋዥ እርምጃዎች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት በግልጽ ዕውቅና የሚያገኝ ደንብ አውጥቶ ሌሎችን አጠቃላይና ልዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን፣ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶችን በማስከበር ረገድ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ልምዶች ጋር ተስማሚ የሆኑ አፍሪካዊ ልምዶችን፣ በአፍሪካ ሀገራት ዕውቅና ያገኙ አጠቃላይ የሕግ መርሆዎችን፤ እንዲሁም ቀዳሚ የሕግ ተሞክሮዎችንና መምሪያዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

### አንቀጽ 62

እያንዳንዱ ይህን ቻርተር የተቀበለ ሀገር ቻርተሩ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በቻርተሩ ዕውቅናና ዋስትና ያገኙ መብቶችንና ነጻነቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ ስለወሰዳቸው ሕግ የማውጣትና ሌሎች እርምጃዎች በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

### አንቀጽ 63

1. ይህ ቻርተር የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት እንዲፈርሙት፣ እንዲያጸድቁት ወይም እንዲቀበሉት ተዘጋጅቷል፡፡
2. የዚህ ቻርተር ማጽደቂያ ወይም መቀበያ ሰነዶች ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ይቀርባሉ፡፡

3. ይህ ቻርተር ከግማሽ በላይ ቁጥር ያላቸው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል ሀገራት የላኩለትን የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነዶች ዋና ጸሐፊው ከተቀበለ ከሦስት ወራት በኋላ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

## ክፍል 3 - አጠቃላይ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 64

1. ይህ ቻርተር በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ በኋላ የኮሚሽኑ አባሎች አግባብነት ባላቸው የቻርተሩ አንቀጾች በሚደነግጉት መሰረት ይመረጣሉ፡፡
2. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ከሦስት ወራት በኋላ የመጀመሪያውን የኮሚሽኑን ስብሰባ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ይጠራል፡፡ ከዚያ በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮሚሽኑ ስብሰባ በኮሚሽኑ ሊቀመንበር ይጠራል፤ ሆኖም ኮሚሽኑ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ 65

ቻርተሩ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በሚያጸድቁት ወይም በሚቀበሉት ሀገራት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው አጽዳቂው ወይም ተቀባዩ ሀገር ያጸደቀበትን ወይም የተቀበለበትን ሰነድ ዋና ጸሐፊው ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ሦስት ወራት ካለፉ ነው፡፡

### አንቀጽ 66

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በልዩ ሁኔታ በተደረጉ ፕሮቶኮሎች ወይም ስምምነቶች ቻርተሩን ማሟላት ይቻላል፡፡

### አንቀጽ 67

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የደረሰውን እያንዳንዱን የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ አባል ሀገራት እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ 68

አንድ ቻርተሩን የተቀበለ ሀገር ቻርተሩ እንዲሻሻል ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት በጽሑፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ቻርተሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡ የቻርተሩን ማሻሻያ ረቂቅ ሁሉም ቻርተሩን የተቀበሉ ሀገራት ካወቁትና ቻርተሩ እንዲሻሻል የቀረበውን ጥያቄ በኃላፊነት በሚከታተለው ሀገር

ጠያቂነት ኮሚሽኑ አስተያየቱን ከሰጠበት በኋላ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ሊመረምረውና ሊወያይበት ይችላል፡፡ ማሻሻያው ቻርተሩን ከተቀበሉ ሀገራት መካከል ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሆኑት ከደገፉት ይጸድቃል፡፡ የማሻሻያ ሰነዱ ማሻሻያውን በተቀበለ በእያንዳንዱ ሀገር ተፈጻሚ የሚሆነው በሀገሩ ሕግ መንግሥታዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት መሠረት ሆኖ ጸሐፊው ሰነዱ ተቀባይነት ማግኘቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ሦስት ወራት ካለፈ በኋላ ነው፡፡

በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አሥራ ስምንተኛው የሀገርና የመንግሥት መሪዎች ጠቅላላ ስብሰባ ይህ ቻርተር ተቀባይነት አግኝቶ ጸድቋል፡፡

እ.አ.አ. ጁን ወር 1981 - ናይሮቢ ኬንያ